# ደንብ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

| | |
|---|---|
| ***ተዛማጅ ሠነዶች፦*** | ACF, ACF-RA, COA, COA-RA, DJA-RA, IOE-RB |
| ***የሚመለከታቸው ጽ/ቤቶች፦*** | የደህንነት እናየህግማስከበር ዋና ሃላፊ፣ የት/ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ ዋና ኃላፊ |

## ጾታዊ ጥቃት በመፈፀም ወንጀል የተመዘገበ ሰዎች MCPS ንብረት ውስጥ የሚስተናገዱበት ሁኔታ

I. **ዓላማ**

በጾታዊ ጥቃት ተከሳሽዝርዝር ውስጥየሚገኝጾታዊ ጥቃት የፈጸመ(ች) አዋቂ ወይም ወጣት ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ሊገባ ስለሚችልባቸው ውስን ሁኔታዎች መመሪያ መደንገግ።

II. **ትርጉም**

A. የሜሪላንድ ጾታዎ ጥቃት የፈጸሙ ወንጀለኞች መዝገብ የሚያዘው በሜሪላንድ ስቴት የህዝብ ደህንነት እና የማረሚያ አገልግሎት ዲፓርትመንት (ዲፓርትመንት) ሲሆን በህግ የተቀመጡ የተወሰኑ የጾታዊ ጥቃት ወንጀሎች ጥፋተኛ ግለሰቦችን መረጃ ይዘረዝራል። መዝገቡ ለማህበረሰብ ተደራሽ ስለሆነ የወንጀለኞችን ዝርዝር ከዚያ ውስጥ ፈልጎ ማግኘት ይቻላል። መምሪያው/ዲፓርትመንቱ ከጎልማሶች የጾታዊ ጥቃት ወንጀለኞች መዝገብ በተለይ ህግ ለማስከበር ዓላማ ለህግ አስከባሪ ሰራተኞች ብቻ ተደራሽ የሆነ በታዳጊዎች ላይ ጾታዊ ጥቃት የፈፀሙ ወንጀለኞችንም ዝርዝር ይይዛል። እዚያ ውስጥ ያለው የወንጀለኞች ዝርዝር ለህዝቡ ወይም ለ MCPS ተደራሽ አይደለም።

B. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)ንብረትማለት፦ ማንኛውም MCPS የሚያስተዳድረው ትምህርት ቤት ወይም MCPS ይዞታ ስር የሚገኙ ወይም የሚተዳደሩ መሬቶችን ጨምሮ ሌሎች መገልገያዎች (ፋሲሊቲ)፣የ MCPS አውቶቡሶች፣ ሌሎች የ MCPS ተሽከርካሪዎች፣እና MCPS እንቅስቃሴ የሚያካሄድበት ቦታ ነው።

C. የሚመለከተው አስተዳዳሪ (አስተዳዳሪ) ማለት፦ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤት ርዕሰ-መምህር ወይም MCPS ንብረት ላይ የሚገኝ በልጆች እንክብካቤ ባለቤትነት የሚካሄድ ተቋም/ፋሲሊቲ ማለት ነው።

D. ለዚህ ደንብ ዓላማ ሲባል የትምህርት አመት ማለት ከጁላይ 1 እስከ ጁን 30 ድረስ ያለው ቀጣዩ የቀን መቁጠርያ/የካላንደር አመት ጊዜ ነው።

E. ጾታዊ ጥቃት በመፈፀም የተመዘገበ ወንጀለኛማለት፦ ግለሰቡ(ቧ) በታዳጊ ልጅ ላይ ጾታዊ ጥቃት የፈጸመ(ች) ወንጀለኛ፣ ሀይልን በመጠቀም ጾታዊ ጥቃት የፈጸመ(ች) ወንጀለኛ፣ የዓይምሮ ህመም ባለበ(ባ)ት ግለሰብ ላይ የጾታዊ ጥቃት የፈጸመ(ች)ወልጀለኛ፣ ወይም ዕድሜያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ ሰዎች ላይ ሌሎች ወንጀሎችን ወይም የልጅ ጠለፋን በመፈጸም የተፈረደበ(ባ)ት ወንጀለኛ በመሆኑ(ኗ) በዲፓርትመንቱ እና በአካባቢው የህግ አስከባሪ አካላት መመዝገብ ያለበ(ባ)ት እና በሜሪላንድ የጾታዊ ጥቃት ወንጀለኛ መዝገብ ውስጥ መመዝገብ ያለበ(ባ)ት ግለሰብን ያመለክታል።

a. የተመዘገበ ወጣት ማለት፦ በጎልማሳ ግለሰብ ቢፈጸም በህግ የተደነገጉ የተወሰኑ የጾታዊ ጥቃት ወንጀሎች ጥሰት ለሚሆን ድርጊት በጥፋተኛነት የተፈረደበ(ባ)ት በሜሪላንድ ስቴት አቃቤምሕግ ትዕዛዝ በጾታዊ ጥቃት የወንጀለኛነት መዝገብ ውስጥ የተካተተ(ች) ዕድሜው(ዋ) ቢያንስ 14 ዓመት የሆነ ግለሰብ ማለት ነው ። በጥፋተኛነት የተወሰነበ(ባ)ት ወጣትየወንጀል ህግ ጥሰት መፈፀሙን በታዳጊ ወጣቶች የፍትሕ ስርአት የተወሰነበ(ባ)ትን ታዳጊ ወጣት ለመግለጽ በታዳጊዎች የፍትህ ስርዓት በሥራ ላይ የዋለ አገላለጽ ነው።

b. የታዳጊ ወጣቶች የፍትሕ ስርአት በተመዝጋቢው(ዋ) ታዳጊ ወጣት ላይ ያሳለፈው የእገዳ ውሳኔ ሲያበቃ፣ወጣቱ(ቷ) ከመዝገቡ ላይ ይሰረዛል/ትሰረዛለች።

## III. ጉዳዩ

ከዚህ በታች A እና B ላይ ከተገለፀው ሁኔታ በስተቀር፣ በጾታዊ ጥቃት የተመዘገበ(ች) ታዳጊ ወጣት ወደ MCPS ትምህርት ቤት ወይም MCPS ንብረት ውስጥ ወደሚገኝ የህጻናት እንክብካቤ ተቋም/ፋሲሊቲ መግባት አይችልም/አትችልም።

### A. የተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ

1. በሜሪላንድ ህግ መሰረት፣ MCPS ትምህርት ቤት ውስጥ ወይም MCPS ንብረት ላይ በሚገኝ የህጻናት እንክብካቤ ተቋም/ፋሲሊቲ ውስጥ የሚማር ተማሪ ያለው/ያላት በጾታዊ ጥቃት የተመዘገበ(ች) ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ጾታዊ ጥቃት በመፈፀም የተመዘገበ(ች) ታዳጊ ወጣት የሚከተሉት ሁለት ሁኔታዎች ከተሟሉ ብቻ ወደዚያ ትምህርት ቤት ወይም የህጻናት እንክብካቤ ተቋም/ፋሲሊቲ ውስጥ መግባት ይችላሉ።

   a. የጾታ ጥቃት በመፈፀም የተመዘገበ(ች) ግለሰብ/ታዳጊ ወጣት በቦታው መገኘት እንደሚፈልጉ እና የጉብኝቱን ዓላማ አስቀድመው ለአስተዳዳሪው ካሳወቁ፣ እና

   b. ከአስተዳዳሪው፣ ከት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ፣ ወይም ከትምህርት ቦርድ ባለፈው የትምህርት ዓመት ልዩ የጽሁፍ ፍቃድ ተሰጥቶ ከሆነ።

2. አስተዳዳሪው እንዲህ ዓይነት ፍቃድ መስጠት ከፈለገ፣ ፍቃዱ በጽሁፍ መሆን አለበት እና የሚከተሉትን ማካተት አለበት፦

   a. ፍቃዱ ለየትኛው ቀን እና ለምን ዓላማ እንደተሰጠ።

   b. ጉብኝቱ የሚካሄድበት በትምህርት ቤት ውስጥ፣ወይም በትምህርት ቤት ይዞታ ላይ ያለ ቦታ።

   c. በጾታዊ ጥቃት የተመዘገበ(ች) ግለሰብ ወይም ሪኮርድ ያለበት ታዳጊ ወጣት ወደ ት/ቤት ግቢ ሲገባ/ስትገባ ማሳወቅ ያለበ(ባ)ት የትምህርት ቤት ሰራተኛ ስም እና አድራሻ።

   d. ወደ ትምህርት ቤት ግቢ የሚገቡት ትርዒት ለመሣተፍ፣በአትሌቲክስ ዝግጅት ለመሣተፍ፣ ወይም በርካታተማሪዎችን በሚያካትት ሌላ ዓይነት ዝግጅት ላይ ለመካፈል ከሆነ፥ ሪኮርድ ያለበ(ባ)ትን ግለሰብ ወይም በጾታዊ ጥቃት የተመዘገበ(ች) ታዳጊ ጋር አብሮ የሚሆን በአስተዳዳሪው ተቀባይነት ያለው ሰው ስም።

3. በጾታዊ ጥቃት ወንጀል የተመዘገበ(ች)በት ሁኔታ አጠራጣሪ ወይም ገደብ ያለው ከሆነ እና የፈቃድ ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ከወሰነ(ች) ሪኮርድ ያለበ(ባ)ት ግለሰብ ለመግባት ፈቃድ እንዲሰጠው ያቀረበ(ች)ውን ጥያቄ የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ ወይም የሕጻናት እንክብካቤ ተቋም/ፋሲሊቲ አስተዳዳሪ ውድቅ ሊያደርግ ይችላል።

B. በመራጭነት የተመዘገበ(ች) ግለሰብ

1. በሜሪላንድ የፕራይመሪ እና አጠቃላይ የምርጫ ቀናት ህዝቡ ለምርጫ ወደ ድምጽ መስጫ ቦታዎች መሄድ ስላለበት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች ለሰራተኞች እና ለተማሪዎች ዝግ ናቸው።

2. የስቴት ህግ በጾታዊ ጥቃት የተመዘገበ(ች) ግለሰብ ወይም ጾታዊ ጥቃት በመፈፀም ሪኮርድ ያለበ(ባ)ት ታዳጊ ወጣት ለመራጭነት በአግባቡ የተመዘገበ(ች) ከሆነ እና የተመዝጋቢው(ዋ) ፣ የምርጫ ጣቢያ/የድምጽ መስጫው ቦታ MCPS ግቢ ውስጥ ከሆነ በምርጫ ቀን ለመምረጥ ወደ MCPS ግቢ እንዲገቡ ይፈቅዳል።

3. በጾታዊ ጥቃት የተመዘገበ(ች) ግለሰብ ለመራጭነት በአግባቡ ከተመዘገበ(ች) እና የተመዝጋቢው የምርጫ ጣቢያ/የድምጽ መስጫ ቦታ MCPS ግቢ ውስጥ ከሆነ አስተዳዳሪው(ዋ)የተመዝጋቢው(ዋ)ን የመምረጥ መብትሊያግድ አይችልም።

C. MCPS ጋር የሚሰሩ የስራ ተቋራጮች እያወቁ ጾታዊ ጥቃት በመፈፀም የተመዘገበ(ች) ግለሰብ ወይም ሪኮርድ ያለበ(ባ)ት ታዳጊ ለትምህርት ቤት ሥራ መቅጠር የለባቸውም። የስራ ተቋራጭ ግዴታዎች MCPS ደንብ DJA-RA፣የመሳሪያዎች ግዥ፣አቅርቦት፣ እና አገልግሎቶች፣እና በግዥ ክፍል የተዘጋጀ ተጨማሪ መመሪያ ላይ ተገልጸዋል።

D. በህግ አስከባሪ የሚሰጥ ማስታወቂያ

1. MCPS በሜሪላንድ ህግ ላይ በተደነገገው መሠረት፥ ግለሰቦች በኃልማሳ የጾታዊ ጥቃት ወንጀለኞች መዝገብ ላይ ወይም በታዳጊ ወጣት የጾታዊ ጥቃት መፈፀማቸው በወንጀለኝነት መዝገብ ላይ ሪኮርድ እንደተያዘባቸው የአካባቢ ህግ አስከባሪዎች ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የማሳወቅ ሀላፊነቶችን የሚዘረዝር የመግባቢያ ሰነድ ከህግ አስከባሪዎች ጋር ያዘጋጃል። እንደዚህ ዓይነት ህጎች የህግ አስከባሪዎች ከጾታዊ ጥቃት ወንጀለኛ የምዝገባ መግለጫ ከተቀበሉ ከሶስት የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በተቻለ ፍጥነት ለት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ የጽሁፍ ማሳሰቢያ እንዲልኩ ያስገድዳሉ።

2. ከአካባቢው የህግ አስከባሪ ክፍል ማስታወቂያ ከደረሰው ከ10 የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካዩ የጾታዊ ጥቃት ፈጻሚ ምዝገባ መግለጫውን የጽሁፍ ማስታወቂያ ለትምህርት ቤቶች ርዕሰ-መምህራን ወይም ሱፐርኢንተንደንቱ ተማሪዎቹን እና ሰራተኞቹን ከጾታዊ ጥቃት ወንጀለኛ ለመጠበቅ አስፈላጊ ነው ብሎ ለሚያስበው ተቆጣጣሪ ስር ለሚሠሩ ወይም MCPS ግቢ ውስጥ ለሚሠሩ የህጻናት እንክብካቤ ተቋም አስተዳዳሪዎች መላክ አለበት።[1]

**IV. ቅደም ተከተል**

በጾታዊ ጥቃት ፈጻሚነት ተመዝጋቢዎች፣ ታዳጊ ወጣት ተመዝጋቢዎች፣ እና የቀድሞ ታዳጊ ወጣት ተመዝጋቢዎች

[1]የተብራራ የሜሪላንድ ኮድ የወንጀል ድርጊት የምዝገባ ሂደት፣ሰክሽን 11-709(b)(1-2)

ትምህርት፡-

A. በጾታዊ ጥቃት ፈጻሚነት የተመዘገቡ ታዳጊ ወጣቶች ጥፋተኛ ተብለው ከተፈረደባቸው እና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በታዳጊ ወጣት አገልግሎት ዲፓርትመንት/Department of Juvenile Services (DJS) ፋሲሊቲ ውስጥ እንዲቆዩ ከተደረገ፣ትምህርታቸውን የሚቀጥሉት በታዳጊ ወጣት አገልግሎት የትምህርት ፕሮግራም/Juvenile Services Education Program (JSEP) ሲሆን ከዚያ በኋላ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪ ሆነው አይመዘገቡም።

B. ታዳጊ ወጣት ሆነው ጾታዊ ጥቃት ፈፅመው የተመዘገቡና በጥፋተኛነት ተፈርዶባቸው የነበሩ ታዳጊዎች ወደ ማህበረሰቡ እንዲመለሱ/እንዲቀላቀሉ ከተደረገ በኋላ፣በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተመዘገቡ ተማሪዎች ሆነው ይቀጥላሉ።

C. በሜሪላንድ ህግ መሰረት፣ MCPS በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አንደኛ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም ለህጻናት እንክብካቤ በሚውል ፋሲሊቲ ውስጥ በጾታዊ ጥቃት ወንጀለኝነት ለተመዘገቡ ጎልማሶች ወይም ታዳጊ ወጣቶች ትምህርት አይሰጥም። ህጉ በጾታዊ ጥቃት ወንጀለኝነት ለተመዘገቡት ከሚከተሉት ቦታዎች በአንዱ ብቻ ትምህርት እንዲሰጥ ይፈቅዳል፡-

    1. ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ውጪ በሆኑ የፕሮግራም አማራጮች፡-

        a. ለልጆች እና ለጎረምሶች/ለኮረዶች የተቋቋመ ሪጅናል ተቋም/Regional Institute for Children and Adolescents (RICA)

        b. በሕግ በተደነገገው መሠረት የተወሰኑ የሕዝብ ያልሆኑ የትምህርት ፕሮግራሞች

    2. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አማራጭ ፕሮግራሞች፡-

        a. በቤት ውስጥ እና በሆስፒታል ውስጥ የሚሰጥ የትምህርት ፕሮግራም (HHT) (ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ውጪ)

        b. በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ የጸደቀ ፕሮግራም (ከአንደኛ ደረጃ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም የሕጻናት እንክብካቤ ካለበት ፋሲሊቲ ውጪ በሆነ በሌላ ቦታ)

D. የታዳጊ ወጣት የፍርድ ቤት ውሳኔ እስከሚያበቃ ድረስ፣ MCPS የት/ቤት ድጋፍ እና ማሻሻል ቢሮ/Office of School Support and Improvement (OSSI) አግባብነት ካላቸው MCPS ቢሮዎች ጋር በመተባበር የተማሪው(ዋ)ን የትምህርት ፕሮግራም የማስተባበር ሃላፊነት አለበት።

    1. ለተማሪው(ዋ) HHT ከመፈቀዱ በፊት ምክንያቱም HHT አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም ስላልሆነ፣ወይም የተማሪን አጠቃላይ የትምህርት ፕሮግራም እንዲተካ የታለመ ወይም የተነደፈ ስላይደለ MCPS ሁሉንም አጠቃላይ የትምህርት ፕሮግራም አማራጮችን መሞከር አለበት። MCPS ደንብ IOE-RB፣በቤት ውስጥ እና በሆስፒታል ውስጥ የሚሰጥ ትምህርት ላይ በተገለጸው መሰረት፣HHT ትምህርት እንዳይከታተሉ የሚከለክላቸው አካላዊ ወይም ስሜታዊ የጤና እክል ላጋጠማቸው ተማሪዎች በዋና የትምህርት ዓይነቶች ላይ ያተኮረ ትምህርት እንዲሰጥ ተደርጎ የተዘጋጀ የአጭር ጊዜ አገልግሎት ነው።

2. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የልዩ ትምህርት ቢሮ ብቁ የሚያደርጋቸው እክል ያለባቸው ታዳጊ ወጣት የጾታዊ ጥቃት ተመዝጋቢዎች ያሉትን የትምህርት አማራጮች ለመለየት RICA ጋር ወይም ህዝባዊ ካልሆኑ የትምህርት ፕሮግራሞች ጋር በቅንጅት መስራት አለበት።

E. ጾታዊ ጥቃት በመፈፀም የተመዘገበ(ች) ታዳጊ ወጣት በፍርድ ቤት ውሳኔ ስር መሆኑ(ኗ) ሲያበቃ፣ ታዳጊው(ዋ) ከመዝገብ ላይ ይሰረዛል/ትሠረዛለች።

1. ከመዝገቡ የተሰረዘ(ች) ተማሪ በመኖሪያ ቤታቸው አካባቢ ባለ ትምህርት ቤት ወይም ተማሪው የፍርድ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ይማርበት/ትማርበት በነበረው ፕሮግራም በድጋሚ መመዝገብ ይችላል/ትችላለች፣ይህ የሚሆነው ግን "የሞንትጎመሪ ካውንቲ ትክክለኛ ነዋሪነት የምዝገባ መስፈርት" የሚያሟሉ ከሆነ ነው።

2. OSSI የእነዚህን ተማሪዎች ምደባ፣ የእያንዳንዳቸውን ጉዳይ አንድ በአንድ እያየ ይገመግማል፣ MCPS የተማሪ ሥነ ምግባር ደንብ ውስጥ ለተገለፀ ጥፋት የዲሲፕሊን እርምጃም ሊወሰድ ይችላል።

**ተዛማጅ ሠነዶች፦** የተብራራ የሜሪላንድ ኮድ/Annotated Code of Maryland, የወንጀል ሂደት አንቀጽ §§11-704, 11-704.1, 11-713, 11-721, 11-722፣የትምህርት አንቀጽ §6-113.2

**ደንቡ የተሻሻለባቸው ጊዜያት፦** አዲስ ደንብ ጁን 12, 2007፣ኦገስት 27, 2024 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ን)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኸውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ። በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድጋጌ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-

U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, oወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ሀምሌ 2024